# አቶ መለስና ብርቱካን ሚደቅሳ !

ከግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ዋሽራ-2 ተብለዉ የሚታወቁ አፍቃሪ ኢሕአዴግ ግለሰብና አቶ ቀለሙ ስሜነህ የሚባሉ አንድ ሰዉ፣ አቶ መለስ ዜናዊ በቅርብ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ በተመለከተ የጻፉትን ጽሁፎች ካነበብኩኝ በኋላ መልስ መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት የሚከተለዉን ለአንባቢያ አቅርቢያለሁ።

እነዚህ ሁለት ወንድሞቼ ለአቶ መለስ ዜናዊ ትልቅ ከበሬታ እንዳላቸዉና እንደሚያደንቋቸዉ ጽፈዋል። ዋሽራ-2 «አቶ መለስ ዜናዊ ለሰላም ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለሕግ የበላይነት የሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት ዳያስፖራዉ ተረድቶ በኢኮኖሚ በማህበረሰባዊና በፖለቲካዉ ዘርፍ ድርሻዉን ያበረክት ዘንድ ጸሎቴና ተስፋዬ ነዉ» ሲሉ አቶ መለስ ዜናዊ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰላም የቆሙ እንደሆኑ ለማስረዳት ሞክረዋል። በእንግሊዘኛና በአማርኛ ቋንቋ መናገር መቻላቸዉን አድንቀዉ ጥያቄ የመመለስ ችሎታቸዉን እንደዉም ከአባማ የበለጠ እንደሆነ ሊነግሩንም ይፈልጋሉ።

አቶ ቀለሙ በበኩላቸዉ አቶ መለስ በሚቀጥለዉ ምርጫ ተወዳደረዉ እስከ 2007 ዓ.ም (2015 እንደፈረንጆች አቆጣጠር) እንደገና ጠቅላይ ሚኒስተር ሆነዉ እንዲገዙ ምርጫቸዉ እንደሆነ ይናገራሉ። እርሳቸዉን ተክቶ ሊሰራ የሚችል ሰዉ እንደሌለና አቶ መለስ ዜናዊ አህጉራዊ መሪ እንደሆኑ በመግለጽ በዚህ ባልተረጋጋ ወቅት መሪ መቀየሩ ጎጂ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። (ኢትዮጵያ አንድ አቶ መለስን ብቻ ያለት ይመስል)

## የአቶ መለስ እንግሊዘኛ

የአቶ መለስ ዜናዊ የእንግሊዘኛ ችሎታ በዋሽራ-2 ከተነሳ አይቀር ጥቂት በዚህ ጉዳይ ላይ ወርወር ላድርግና ወደ ዋናዉ ቁም ነገር ልመለስ።

በመጀመሪያ ደረጃ የአቶ መለስ ዜናዊ በስብሰባዎች ላይ በእንግሊዘኛ መናገር የሚያኮራና የሚደነቅ ሳይሆን የሚያሳፍርና የአገርን ባህል የሚያዋርድ ነዉ። የቻይናዉ መሪ ሁ ጂን ታዉ ዉጭ አገር ሲንበኙ በማንደሪን ነዉ የሚናገሩት። ቭላዲሚር ፑቲን በራሽይኛ ነዉ የሚናገሩት። ኒኮላይ ሳርኩዚ በፈረንሳይኛ ነዉ የሚናገሩት፡፡ የኢራኑ አህማዲኒጃድ በፋርሲ ነዉ የሚናገሩት። ኢትዮጵያ የራሷ በርካታ ቋንቋዎች እያሏት በአለም ከፍተኛ መድረኮች በእንግሊዘኛ መናገር አሳፋሪ ነዉ።

አቶ መለስ እንግሊዘኛቸዉን ማሳየት ከፈለጉ እንግሊዝ ወይ አሜሪካ ጥገኝነት ጠይቀዉ የአንዱ አውራጃ ተወዳዳሪ ሆነዉ መለፈፍ ይችላሉ። ለብሄር ብሄረሰቦች መብት ቆሚያለሁ እያሉ የኢትዮጵያን ባህል እንደ አንድ ብሄር ለአለሙ ሕብረተሰብ ለማስተዋወቅ ማፈራቸዉ አሳዛኝ ነዉ። እሺ በአማርኛ አይናገሩ ... **አፋቸዉን የፈቱበት የትግርኛ ቋንቋ ምን ወጣለት?**

## አቶ መለስና የሕግ የበላይነት

ስለ አቶ መለስ ዜናዊ በአንዳንድ ማዕዘናት ጥሩ ነገር ሲነግር እሰማ ነበር። አብረዋቸዉ ያሉ አክራሪዎች ስላስቸገሯቸዉ እንጂ ለዘብተኛና (ሞደሬት) አስተዋይ እንደሆኑ ከመስማቴ የተነሳ አቶ መለስ ዜናዊ ይሰሙ እንደሆን በሚል ግምት ሶስት ጊዜ ግልጽ ደብዳቤ ጽፌላቸዋለሁ።

እነ አቶ ዋሽራ እንዳሉት አቶ መለስ አስተዋይና በሳል መሪ ቢሆኑ ኖሮ ሁላችንም ደስ ባለን ነበር። አገራችንን የሚመራ ሰዉ አስተዋይና ለህዝብ ሃሳቢ የሆነ እለታ አገር ትለማለች። በዚህም ምክንያት ነዉ በአንዱ ጽሁፌ ለአቶ መለስ እግዚአብሄር ማስተዋል እንዲሰጣቸዉ ጸሎት እንደማደርግም የገለጽኩት። በእጃቸዉ ትልቅ ሃላፊነት እንደመጨበጣቸዉ የሚወስኑት ዉሳኔ በአገር ደርጃ ትልቅ ጥፋት ሊያመጣም እንዲሚችል በማሰብ እግዚአብሄር በዉሳኒያቸዉ ጣልቃ እንዲገባ ተማጽኛለሁ።

ይህ በዚህ እንዳለ አቶ መለስ በቅርብ ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ስሰማ እኝህ ሰዉ ድርብ ገጽታ እንዳላቸዉ ለማየት ችያለሁ። የተናገሩትንም ስመዝነዉ እነ ዋሽራ እንዳሉት የሚደነቅን ማስተዋል የሞላዉ ንግግር ሳይሆን የቀለለና ፣ይቀርታ አድርጉልኝ፣ የተራ ዱርዬ አነጋገር ሆኖ ነዉ ያገኘሁት።

ለምሳሌ ስለ ሶማሊያና በሚሊዮን የሞቆጠር ሕዝብ እየተራበ ባለበት ሁኔታ 11.8 % የሚሆነዉ አስቂኝ የኢኮኖሚ እድገትን ለጊዜዉ ልተወዉና ስለሕግ የበላይነት አቶ መለስ የተናገሩትን ላንሳ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን “ሴትየዋ” በሚል ጨዋነት የጎደለዉ አጠራር በመጥራት ነበር አቶ መለስ በአደባባይ ሲዘልፉ የነበሩት። የወይዘሪቷ መታሰር የሕግ ጉዳይ እንደሆነና ሕግ የበላይ መሆን ስላለበት “ሴትየዋ» መታሰር እንዳለባቸዉ በጨዉ አይናቸዉን አጥበዉ ነበር አቶ መለስ በድፍረት የነገሩን።

አቶ መለስ እንዳሉት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሕግ አልጣሱም። ጠመንጃ አላነሱም። ሰዉ አልገደሉም። እንደዉ «ወያኔ ጠላት አይደለም« ብለዉ በጋራ እርቀ ሰላም እንዲወርድና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የሚጥሩ፣ ችግሮችን በጠመንጃ የመፍታት ባህል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ እንዲወገድ የሚታገሉ የመርህና የፍትህ ሴት ናቸዉ።

ታዲያ አቶ መለስ ለሰላም የቆመን ሰዉ ማሰር ሕግን ማስከበር ነዉ ብለዉ ሲናገሩ ሰዉ ምን ይለኛል ብለዉ አያፍሩም ? እርሳቸዉ በቀጥታ የሚያዙት የፌደራል ፖሊስ ወጠምሻ እንስሶች የሰባ ስምንት አመት አባትን በሰደፍ ሲደበድቡ፣ ሴት ልጅን ለአሥር እያዋከቡና እያንገላቱ ሲወስዱ ይህ ነዉ ሕግን ማስከበር ? ከአምሳ ቀናት በላይ ጨለማ ቤት ዉስጥ አንዲትን ሴት ማሰርና ማሰቃየት ይህ ነዉ ሕግን ማስከበር ? ጠበቃ ሃኪም ዘመድና ወዳጅ ወ/ት ብርቱካንን ሚደቅሳን እንዳያያቸዉ መከልከሉ ነዉ ሕግን ማስከበር ? ጉዳያቸዉን ፍርድ ቤት እንዳይወስዱ ማገድና ከፍርድ ቤት በላይ መሆኑ ነዉ ሕግን ማስከበርና ለሕግ የበላይነት መቆም?

በኢትዮጵያ የበላይ ሕግ ሕገ መንግስቱ ነዉ። አቶ መለስ «ሕገ መንግስት» የሚሉት ሌላ ሰነድ ኖሯቸዉ ከሆነ ሌላ ነገር ነዉ። አብዛኞቻችን ግን የምናዉቀዉና ለሕዝብ ይፋ የሆነዉ የሕግ መንግስቱ ሰነድ በግልጽ እንደሚያስቀምጠዉ ዜጎች ጉዳያቸዉን ፍርድ ቤት የማቅረብ ሙሉ መብት አላቸዉ። አንድ ሰዉ ከታሰረ ደግሞ በዘመድ፣ በጠበቃ፣ በሐኪም በመንፈሳዊ አባቶች መጎብኘት እንደሚችል ሕጉ ይደነግጋል።

ታዲያ ሕገ መንግስቱ የሚለዉ ይህ ሆኖ እያለ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እንዲሰቃዩ፣ በጨለማ ቤት እንዲቀመጡና ፈረንጆች ቶርቸር የሚሉት እንዲደርስባቸዉ መደረጉ ሕግን ማስከበር ነዉ ?

**እኔ ይህን ሕግ ማስከበር አልለዉም። ይህን ሌላ ትርጉም አልሰጠዉም። ይህ ትልቅ ዉንብድና ነዉ የምለዉ።**

**አቶ መለስ በወ/ት ብርቱካን ላይ ለምን ጨከኑ ?**

አቶ መለስ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ ይህን አይነት የጭከና እርምጃ የወሰዱት ለምን እንደሆነ አይገባኝም። ከሁሉም አቅጣጫዎች አገናዝቤ የደረስኩበት ድምዳሜ ቢኖር ያለ ምንም ጥርጥር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እያደረጉት ያለዉ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አቶ መለስን ስላስፈራቸዉ ነዉ።

አቶ መለስ የቅንጅት መሪዎችን ለሃያ ወራት አስረዉ የፓርቲዉን ንብረት ዘርፈዉ «ቅንጅትን አጠፋን፣ ተሳካልን» ብለዉ ጮቤ እየረገጡ ነበር። እኔ ባለሁበት ከተማ የሚኖሩ አቶ መዝገበ ክርስቶስ የሚባሉ አንድ አፍቃሪ መለስ ዜናዊ ሰዉ «ቅንጅት መነሳት እስከማይችል ድረስ ፈርሷል« ሲሉ የአይጋ ፎረሙ አቶ ዘሩ ሃጎስ ደግሞ «ቅንጅት ሞቷል« ብለዉ የጻፉትን ማስታወሱ ብቻ ይበቃል።

በቅንጅት ስም መንቀሳቀስ እንዳይቻል፣ የቅንጅትን ስም አሁን ድራሻቸዉ የት እንዳለ ለማይታወቀዉ ለእነ አቶ አየለ ጫሚሶ ፣ የቅንጅትን አርማ ደግሞ ለአቶ መለስ አጋር የአቶ ልደቱ ቡድን በመሰጠቱ «ቅንጅት» የተባለ ነገር እንዳይኖር የጡንቻ እርምጃ አቶ መለስ ዜናዊ ሳያቅማሙ ነዉ የወሰዱት።

በእንደዚህ አይነቱ ከባድ ሁኔታ፣ በአሜሪካ ኑሮን መስርቶ በምቾት ከመኖር ይልቅ በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሕዝባቸዉ ጋር ትግልን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መቀጠሉን መረጡ። እዚህ እዚያ እያሉ የወዳደቀዉን አንስተዉ በቀድሞ ቅንጅት አላማና ራዕይ የሚንቀሳቀስ ጠንካራ ድርጅት አብረዋቸዉ ከታሰሩ እንደ እንጂነር ግዛቸዉ፣ ዶር ያእቆብ ኃይለማሪያም፣ አቶ አሥራት ጣሴ፣ ዶ.ር ኃይሉ አርዓያ፣ አቶ ስለሺ ጤና ፣ አቶ ታምራት ታረቀኝና ሌሎች አንጋፋ መሪዎች ጋር በመሆን መሰረቱ። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በሚል ስም ሕገ መንግስቱ በሚፈቅደዉ መሰረት ሰላማዊና ሕጋዊ እንቅስቃሴ ጀመሩ። በሊቀመንበርነት የሚመሩት የአንድነት ፓርቲ ሕጋዊ ፈቃድ ባገኘ በስድስት ወር ዉስጥ ብቻ በየገጠሩ ተሰማርቶ ሕዝቡን ማደራጀት ቀጠለ። አምሳ ሰዎች አይመጡበትም የተባለለት በአዲስ አበባ ሙብራት ኃይል አዳራሽ የተደረገዉ ስብሰባ ከአምስት ሺህ በላይ ህዝብ ሆ ብሎ መጣ።

የዘረኝነትና የጥላቻ ፖለቲካ እንዲጠፋ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ባደረጉት ጥረት በትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ ከፍተኛ ፍቅርና አድናቆት አተረፉ። እነ አቶ መለስ ባለፈዉ ምርጫ “ኢንተርሃዉሜ » እያሉ የትግራይን ሕዝብ ለማስፈራራት የተጠቀሙበትን ርካሽ ታክቲክ ዜሮ አገቡባቸዉ። የትግራይ ሕዝብ ከሶስት አመት በፊት

እንደነበረዉ በፍርሃት ወደ ሕወሃት እንዳይጠጋ አማራጭን አቀረቡለት።

አሁን የትግራይ ሕዝብ አንድነትን ይዞ የተነሳዉና የፍቅርን ፖለቲካ የሚያራምደዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመሩት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ እንደ አማራጭ ቀርቦለታል። አሁን የትግራይ ህዝብ ለሕግ የበላይነትና ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመዉ የአረና ትግራይ ለሉዓላዊነት የተሰኘዉ ድርጅት እድነ አማራጭ ቀርቦለታል። በዚህም ምክንያት ቆሻሻ የዘር ፖለቲካ በመጠቀም ሕዝብ እንዲደግፋቸዉ የማድረግን ጨዋታ አቶ መለስ ዜናዊ መጫወት ከአሁን በኋላ የምይችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል።

«አማራና ኦሮሞ» እያሉ ከሰባ በመቶ በላይ የሚሆነዉን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር ለመከፋፈል በነ አቶ መለስ የሚረጨዉን መርዝ እነብርቱካን ሚደቅሳ ከነዶር መራራ ጉዲናና ዶር ቡልቻ ደምቀሳ ከመሳሰሉት ጋር በጋራ በመስራት ማርከሻ ያዘጋጁለት ሲሆን ይህም ለነአቶ መለስ ትልቅ ራስ ምታት ለቋል።

ሕዝብን የማደራጀት፣ በራሱ እንዲተማመንና እርስ በርሱ በዘር ሳይከፋፈል እንዲያያዝ የማድርግ ፖለቲካ የሥርዓታቸዉ መጨረሻ መሆኑን አቶ መለስ የተገነዘቡ በመሆናችዉ የዚህ ፖለቲካ አራማጅ ፓርቲ መሪን ማሰርና ጸጥ ከማሰኘት ዉጭ ሌላ አማራጭ አላገኙለትም። ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ጥይት ሳትተኩስ፣ በአደባባይ ዘራፍ ሳትል በፍቅር ስለት ትሰነጣጥቃቸዉ ጀመር። ይች ሴት እንድትቆም መደረግ ነበረበት።

### አቶ መለስ በጭንቅላታቸዉ ቢተማመኑ ኖሮ...

የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ፖለቲካ በሰለጠነዉ በዲሞክራሲያዊ መንገድ መቋቋም አቶ መለስ ዜናዊ አልቻሉም። ብቃቱ፣ ብስለቱ፣ ጭንቅላቱ የላቸዉም። እንደ ጨዋ ልዩነቶችን በሕዝብ ፊት አቅርበዉ ሃሳባቸዉ በሕዝብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረጉን አልፈለጉትም። ለምን በራሳቸዉ አይተማመኑም።እራሳቸዉን ይጠራጠራሉ። ከራሳቸዉ ጋር የተጣሉ ናቸዉ። (አብዛኞቻችን እንደምናስታወሰዉ «አስተዋዩ» አቶ መለስ ከሶስት አመት በፊት በተደረጉ የፖለቲካ ክርክሮች አልተሳተፉም ነበር። )

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳያቸዉን በሕግ ፊት ለማቅረብ እንኳን ቢጠይቁ፣ አቶ መለስ እራሳቸዉ የሚቆጣጠሩትን ፍርድ ቤት እንኳን አላመኑትም። ተመልከቱ እንግዲህ .... እኝህን ሰዉ ነዉ እነ ዋሽራ አስተዋይ በሳል መሪ የሚሉን ?

ይልቅ አቶ ቀለሙም ሆነ አቶ ዋሽራም በምዕራባዊዉ አለም ዲሞክራሲን የተማሩ እንደመሆናቸዉ፣ በአቶ መለስ ዜናዊ የሚተማመኑና በሳል አርቆ አስተዋይ መሪ ናቸዉ የሚሉን ከሆነ.... ብዙም ከኛ ጋር መጨቃጨቅ የለባቸዉም። እስቲ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያለአንዳንች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ ይጠይቁና ወ/ት ብርቱካን ነጻና ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ አጀንዳቸዉን ይዘዉ ከአቶ መለስ ጋር በሕዝብ ፊት ይቅረቡ ? እስቲ አቶ መለስ አስቀድመዉ ጥያቄ ለጋዜጠኞች እያቀረቡ ሳይሆን በገለልተኛ ሞደሬተር ከወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጋር የፖለቲካ ክርክር ያድርጉ ? እስቲ ስድስቱን ቀን እርሳቸዉ ይወሰዱትና አንዱን ቀን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ፓርቲያቸዉ በሕዝብ መገናኛ ሚዲያዎች የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸዉን ለሕዝብ እንዲያሰሙ ይፈቀድላቸዉ ? እንግዲህ አስቡት አንድ ለስድስት ማለት ነዉ ... ። መልሱን ለእነ ዋሽራ እተዋለሁ።

በመጨረሻ አቶ መለስ አንድ በተናገሩት አስቂኝ ነገር ላይ አንድ ብዬ ላቁም። አቶ መለስ በዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያን የፈለገ በየኤምባሲዉ ቢጮሁ ብርቱካንን ማስፈታት እንደማይችሉ ተናግረዋል።

ከአምሳ ቀናት በላይ ቶርቸር ቢደረጉም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለአላማችዉና ለኢትዮጵያ ህዝብ የቆሙ ቁርጠኛ መሪ መሆናቸዉን ያሳዩ ጀግና ሴት ናቸዉ። የአምባሳደር እምሩን አባባል ልዋስና ወ/ት ብርቱካን የኢትዮጵያ እምቤት ናቸዉ። አቶ መለስ ዜናዊ ለጊዜዉ በያዙት ጠመንጃ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሥጋ ላይ ጉዳት ቢያደርሱም የእኝህ ሴትን መንፈስ ግን ማስርና መጉዳት አይችሉም።

አቶ መለስ አላወቁትም እንጂ በደህንነት አባሎቻቸዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሰዉ እንዳያነጋገሩ ቢያግዱም በሚሊዮን የምንቆጠር ኢትዮጵያዉያን ከወ/ት ብርቱካን ጋር በመንፈስ እየተነጋገርን ነዉ። ኢትዮጵያውያን የሚሉትን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያዳምጣሉ። እርሳቸዉ የሚሉትንም እኛ እናዳምጣለን። ወ/ት ብርቱካን በዝምታቸዉና ኢፍትሃዊነትን እምቢ በማለታቸዉ የሚያስተላልፉት የዲሞክራሲ የፍትህ የኢትዮጵያዊነትና የትግል መልዕክት በጎላ ሁኔታ እየደረሰን ነዉ። እኛም ከርሳቸዉ ጋር ትግሉን እናጧጡፋለን። እርሳችዉ የለኮሱትን ችቦ የበለጠ እናቀጣጥለዋለን።

አቶ መለስ ባይቀልዱና እራሳቸዉን መሳቂያ ባያደርጉ ይሻላቸዋል። ወደዱም ጠሉም ወ/ት ብርቱካን

ሚደቅሳ ይፈታሉ። እኔን ጨምሮ በአሥር ሚሊዮን የምንቆጠር ኢትዮጵያዉያን የማንተኛበትና የማናንቀላፋበት ጉዳይ ነዉ። እንደ ደራርቱ ቱሉ በክብር የኢትዮጵያን ባንዲራ ለብሰዉ እህታችን ከቃሊቲ ይወጣሉ። ይህንንም በቅርብ ያዩታል።